ቁጥር አብክመ/ጠ/ፍ/ዳ/284/14

ቀን 09/07/2014 ዓ.ም

ለሁሉም ከፍ/ፍ/ቤቶች ን/ጉባኤ ሰብሳቢዎች

ባሉበት

የ---------- ድርሻ

ለ---------- ምድብ ችሎት

ባሉበት

ጉዳዩ፣ የጉባኤ ውሳኔ ማሳወቅን ይመለከታል፣

የአብክመ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መጋቢት 2 እና 3 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ስለ ዳኞች እና የጉባኤ ተሿሚዎች የዓመት እረፍት ፈቃድ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ፈቃዶች አሰጣጥን በተመለከተ የቀረበለትን የውሳኔ ኃሳብ መርምሮ እና ሰፊ ውይይት አካሂዶ ወደፊት ዘላቂ መመሪያ በክልሉ የዳ/አስተዳደር ወጥቶ ተግባራዊ እስከሚሆን ድረስ በሚከተለው መልኩ እየተሰራ እንዲቆይ ሲል ወስኗል፡፡

1. የዳኞች ዓመታዊ ፈቃድ በተለመደው አግባብ ፍ/ቤቶች በሚዘጉበት ወቅት እየተሰጠ እንዲቆይ፣
2. የዳኞች ከዓመት እረፍት ውጭ የሆኑ ልዩ ልዩ ፈቃዶች እና የጉባኤ ተሿሚዎች የዓመት ፈቃድ እንዲሁም ሌሎች ልዩ ልዩ ፈቃዶች ደግሞ በመንግስት ሰራተኞች የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ መሰረት እየተሰጠ እንዲቆይ ሲል የወሰነ ስለሆነ በዚሁ አግባብ ተግባራዊ እንዲደረግ ማስፈለጉን አስታውቃለሁ፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

አብዩ ካሳሁን
የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዘዳንት

ግልባጭ//

- ለፕሬዚደንት ጽ/ቤት
- ለም/ፕሬዚደንት ጽ/ቤት
- ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት
- ለዳኞች አስ/የሰ/ሃ/ዳይሬክተሬት
- ለሰበር ዳኝ/አገ/አሰ/ ዋና የስራ ሂደት
- ለፍትሃብሄር ዳኝ/አገ/አሰ/ ዋና የስራ ሂደት
- ለወንጀል ዳኝ/አገ/አሰ/ ዋና የስራ ሂደት

ጠ/ፍ/ቤት

ቅ/ም